# “ያለ ዴሞክራሲ  እድገት ማስመዝገብ አይችልም”

ገበየሁ  ፍርድያውቃል  01/09/14

## መግቢያ

የቀድሞው ጠቅላይ ሚ/ር አቶ መለስ ዜናዊ ህልፈትን ተከትሎ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ሃይለማሪያም ደሳለኝ አመራሩን ሲረከቡ በአገሪቱ የተጀመሩ እድገትና የልማት ስራዎች በምን መልክ ይቀጥሉ የሆን? በማለት ዓለም በቅርበት ይከታተል ነበር። ባለፉት አስርት አመታት በኢትዮጵያ ለተመዘገበው  የኢኮኖሚ እድገት አቶ መለስ ዜናዊ ትልቅ ድርሻ እንዳላቸው ይታወቃል። እንደ አለም ባንክ መረጃ ባለፉት አስር አመታት የአፍሪካ አገራት በአማካይ  የ5.4 በመቶ የአኮኖሚ እድገት ሲያስመዘግቡ በአንፃሩ ኢትዮጵያ በአማካኝ 9.9 በመቶ እድገት በማስመዘገብ  ውጤታማ መሆን ችላለች።

በኢኮኖሚ እድገትና በሌሎች ጉዳዮች  የኒው አፍሪካ መፅሄት ጋዜጠኛ  ዳሬን ሞር በአዲስ አበባ  ከጠቅላይ ሚኒስትር አቶ ሃይለማሪያም ደሳለኝ ጋር ቃለ ምልልስ አድርጓል። ይህን ቃለ ምልልስ ለአማርኛ አንባቢዎች እንዲያመች በሚል እንደሚከተለው ወደ አማርኛ መልሼዋለሁ።

## “ያለ ዴሞክራሲ  እድገት ማስመዝገብ አይችልም”

**ጥያቄ፣** እጅግ ጠንካራና ትልቅ ሰብዕና ያላቸውን የቀድሞውን  ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊን ተክተው የጠቅላይ ሚኒስትርነትን ቦታ ይዘዋል። እርሶዎ ይህን የጠቅላይ ሚኒስትርነትን  ቦታ ሲረከቡ የነበርዎን  ስሜት ቢያብራሩልኝ?

ጠ/ሚ- ይህን ትልቅ የሃላፊነት ቦታ ልይዝ የቻልኩት በፓርቲዬ ውሳኔ ነው። በርግጥ ትልቅ ስብእና የነበራቸውን ሰው ተከትሎ ወደ ሃላፊነት መምጣት የሚከብድ ነገር ቢሆንም ጠቅላይ ሚኒስትር መለስ ዜናዊ በአገራችን ያለውን አሰራር ተቋማዊ እንዲሆን አድረገውታል። እንዲሁም በጣም በሳል ፓርቲ ያለን በመሆኑ ጠንካራ የመንግስት ተቋማትን መገንባት በመቻላችን በቀላሉ የቀደሞውን ጠቅላይ ሚኒስትር ፈለግ መከተል ችያለሁ።

በሌላ በኩል ከጊዜ ጋር ተለዋወጭና አዳዲስ የሆኑ ነገሮችን አካቶ መስራትን በተመለከተም ግልፅ የሆኑ ፖሊሲዎችና ስትራቴጂዎች የተቀመጡ በመሆኑ አስቸጋሪ ሁኔታዎች አልተፈጠሩም። በርግጥ እኔ መሪ ብሆንም ስራዬን የማከናውነው ከባልደረቦቼ ጋር በመመካከር ነው ። ስራው ፈታኝ ቢሆንም ብዙ ጥሩ ነገሮችም ያሉ በመሆኑም የአቶ መለስ ዜናዊን የእድገት ራዕይ ማስቀጠል ተችሏል።

**ጥያቄ፣** እርስዎ የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትርነት ዳራና ልምድ ያለዎት ነዎት። ይህ ልምድዎ አሁን ላሉበት የስራ ሃለፊነት ምን ያህል አጋዥ ነው ብለው ያምናሉ?

ጠ/ሚ- ወደዚህ ቢሮ ለመምጣት የውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር መሆን የመጨረሻ የስራ ልምዴ ይሁን እንጂ ከዚያ በፊት በተለያዩ የስራ ሃላፊነት ቦታዎች አገልግያለሁ፣ የደቡብ ብሄሮች፣ ብሄረሰቦችና ህዝቦች ክልል ፕሬዝዳንት፣ የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር የማህበራዊ ጉዳይ አማካሪ እንዲሁም የውሃ ቴክኖሎጂ ኢንስቲቲዩት ዲን በመሆን በማገልገሌ በርካታ የተለያዩ ልምዶችን ማካበት ችያለሁ።

የውጭ ጉዳይ ሚኒስትርነት ያገኘሁት ልምድ ለአሁኑ ስራዬ እጅግ ጠቃሚ ነው። የውጭ ጉዳይ ፖሊሲያችን የሚመነጨው የውስጥ ጉዳያችንን መሰረት በማድረግ በኢኮኖሚ ዲፕሎማሲ መርህ ላይ የተመሰረተና ድህነትን ማጥፋት ላይ ያተኮረ ነው።

እንዲሁም የውጭ ፖሊሲያችን በምስራቅ አፍሪካ አካባቢ ፀጥታ ጉዳዮችን እልባት በመስጠትና የአካባቢውን አገራት በጋራ ጥቅም ማስተሳሰር ላይ ያተኩራል። የፀጥታ

ጉዳይን በተመለከተም ግልፅ በሆነው ፖሊሲያችን ከአገራችን ባሻገር ሰላምን በቀንዱ የአካባቢ ማስፈን ተችሏል። በመንግስቴ በግልፅ የተቀመጠው የውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ለስራዬ መቃናትና ቀጣይነት እጅግ እንዳገዘኝ ይሰማኛል።

**ጥያቄ፣** የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር አቶ መለስ ዜናዊ ትልቅ ትኩረት ድህነትን ማጥፋትና እድገትን ማፋጠን ስለነበር ኢትዮጵያ ፈጣንና ቀጣይነት ባለው እድገት በማስመዝገብ በአለም የምትታወቅ አገር ለመሆን በቅታለች። እርሶዎስ ይህን የተጀመረ እድገት ለማስቀጠል ምን አይነት መሰረታዊ የሆኑ ፖሊሲዎች ለመተግበር አስበዋል?

**ጠ/ሚ-** የቀድሞው ጠቅላይ ሚኒስትር ባለፉት አስር አመታት አገራችን ፈጣንና ቀጣይነት ያለው የኢኮኖሚ እድገት እንድታስመዘግብ ትልቅ ድርሻ አበርክተዋል። አሁንም ይህን እድገት ለማሰቀጠል ጠንክረን በመስራት በፖሊሲያችን ላይ እንደተቀመጠው የአገራችንን ኢኮኖሚ ትራንስፎርም ማድረግ ይኖርብናል። በአነሰተኛ መሬቶች ላይ የሚካሄደውን የግብርና ስራችንን ውጤታማ በማድረግ ረገድ የተለያዩ ግበአቶችንና ዘመናዊ አስተራረስን በመጠቀማችን ምርትን ማሳደግ ችለናል። እንዲሁም ኮሜርሺያል (ሰፋፊ) እርሻዎችን በማስፋፋትና ገበያ ተኮር የሆኑ ምርቶችን በማምረት ላይ እንገኛለን። ግብርና ለአገራችን ኢኮኖሚ እድገት ትልቁን ሚና የመጫወት እምቅ አቅም ያለው ዘርፍ በመሆኑ ትኩረት ተሰጥቶታል። አገራችን በግብርናው ዘርፍ ከፍተኛ አቅም ያላት በመሆኑ የአቅርቦት ክፍተታችንን በመቅረፍ የኢኮኖሚ እድገታችን ማረጋገጥ እንችላለን።

የአገራችን ፖሊሲ የሚያተኩረው መሰረተ ሰፊ የሆነውን የግብርና ዘርፉ በማሳደግ የአግሮ ፕሮሰሲንግ እንዲስፋፋ በማድረግ ብሎም ቀላል ኢንዱስትሪዎች እንዲስፋፉ ማድረግ ላይ ነው። አግሮ ፕሮሰሲንግን በማስፋፋት ቀላል ኢንዲስትሪ የሆኑትን የጨርቃ ጨርቅ፣ የስፌት፣ የቆዳና የቆዳ ውጤቶች፣ የታሸጉ ምግቦችና መጠጦችን በማምረት የገበያ ትስስር መፍጠር ይኖርብናል። እነዚህ ፋብሪካዎች

የግብርና ምርቱን በቀጥታ የሚጠቀሙ በመሆናቸው ለማስፋፋት ከፍተኛ ወጪን የሚጠይቁ አይደሉም።

በአገራችን የግብርናው ዘርፍ ሰፊና ሁሉን አቀፍ ዘርፍ በመሆኑ በዚህ ዘርፍ ቀጣይነት ያለው እድገት ማስመዝገብ መቻላችን የአገሪቱን ኤኮኖሚም እድገት ቀጣይነት እንዲኖረው አድርጎታል ማለት ይቻላል። ብዙ ገንዘብ በሚጠይቁ ዘርፎች ላይ ተንጠልጥለን እድገት እናስመዝግብ ብንል ኖሮ የአገራችን እድገት ቀጣይነት ሊኖረው አይችልም ነበር። ምክንያቱም ሌሎች ዘርፎች ከፍተኛ ካፒታል የሚጠይቁ በመሆናቸው ለታዳጊ አገራት የሚከብዱ ናቸው። የእኛ የእድገት ስትራቴጂ ትኩርት የሚያደርገው አዋጪ የሆኑ የእርሻና የማኑፋክቸሪንግ ዘርፍን በማስፋፋት ወደ ኢንደስትሪ ማምራት ላይ ነው።

**ጥያቄ፣** ኢትዮጵያ ሰፋፊ የእርሻ መሬቶችን ለውጭ ባለሀብቶች በሊዝ በማከራየቷ ምክንያት አንዳንድ ክሶች የቀርቡባታል። አገሪቱ ይህን ሰፋፊ የእርሻ መሬቶችን ለባለሃብቶች የመስጠት ፍላጎትና የአካባቢው ነባር ነዋሪዎችን ፍላጎት እንዴት ያጣጥሙታል?

**ጠ/ሚ-** ተጨባጭ የሆነው የአገራችን ሁኔታ እንደሚያሳየው በአነስተኛ ገበሬዎች የተያዘው የእርሻ መሬት ሶስት ሚሊዮን ሄክታር ሲሆን ከ80 ፐርሰንት በላይ የሆነውን የግብርና ምርታችንንም ይሸፍናል። እኛ ደግሞ አሁን ለውጭ ባለሃብቶች የሰጠነው መሬት ከአራት መቶ ሺህ ሄክታር የማይበልጥ መሆኑና አገሪቱ ገና ሊታረስ የሚችል እጅግ በጣም ሰፊ መሬት ያላት ከመሆኑ አንፃር ህዝባችን ከውጭ ሚዲያ በሚሰማው የተሳሳተ መረጃ ግራ መጋባት የለበትም። የውጭ ሚዲያዎች ይህን ጉዳይ አጀንዳቸው ያደረጉበት የራሳቸው ምክንያት ስለሚኖራቸው ነው።

እኛ ለባለሀብቶች የሰጠነው መሬት በማንም ያልተያዘና ጠፍ የሆነን ነው። በህዝባችን ጥቅም ላይ ያልዋለና ጠፍ መሬት ባለሃብቶች ቢያለሙት ክፋቱ ምኑ ላይ ነው? ይህ መሬት ቢለማ ለሁሉም ጥቅም ስለሚሰጥ አገርን ማሳደግ ይቻለል።

እንደነዚህ ያሉ ሰፋፊ እርሻዎችን ማልማት በምዕራቡ ሆነ በእስያ የተለመደ አሰራርና ለእድገት እንደ አንድ ግብአት ተደርጎ የሚወሰድ ነው፤ ታዲያ በኢትዮጵያስ እንዲህ ያለው ነገር ቢተገበር ምን ክፋት አለው?

**ጥያቄ፣** የኢትዮጵያ ህዝብ ቁጥር በፍጥነት በማደግ ላይ በመሆኑ ሰፋፊ የእርሻ መሬቶች በአግባብ መያዝ ያስፈልጋታል። በፍጥነት የሚያድገው የኢትዮጵያ ህዝብ ቁጥር በፖሊሲያችሁ ላይ ያሚያመጣው ተፅእኖ ምንድነው ይላሉ?

**ጠ/ሚ-** የህዝብ ቁጥር መጨመር እንደ አተያይህና እንዳያያዝህ የሚሆን ነገር ነው። የህዝብ ቁጥርን በአግባቡ የምትጠቀምበት ከሆነ ለኢትዮጵያም እንዲሁም ለአፍሪካ ትልቅ አቅም ይፈጥራል። አገሬ እጅግ ብዙ የሆነ ወጣት አላት፤ ከህዝባችን ከ60 በመቶው በላይ ከ15 ዓመት በታች የሆነ ወጣት ሃይል ነው። ይህን ወጣት ሃይል በአግባቡ መጠቀም ከተቻለ ትልቅ ሀብት ነው።

ወጣቶቻችንን በሙያ ኮሌጆቻችን እንዲሁም በዩኒቨርሲቲዎቻችን የተለያዩ የሙያ ክህሎት እንዲያገኙ ለማድረግ ስልጠናዎች እየሰጠን ነው። ይህ ሃይል ተገቢውን ስልጠና ማግኘት ከቻለ ትልቅ ሀብት ነው። መንግስትም ለዚህ ወጣት ሃይል የተለያዩ የስራ እድሎችን እያመቻቸ ይገኛል። ይህን ማድረግ ከተቻለ ወጣት ሃይል ለአገር ትልቅ ሃብት ነው። ይህን ማድረግ ካልተቻለ ግን ውጤቱ በተቃራኒው ሊሆን ይችላል።

**ጥያቄ፣** አብዛሃነትን በተመለከተ፤ ኢትዮጵያ ልዩ የሆነ የፌዴራሊዝም ስርዓትን እንዴት አሰፈነች፣ እንዴትስ የተለያዩ ብሄረሰቦቿን ማስተሳሰር ቻለች?

**ጠ/ሚ-** በቅድሚያ የኢትዮጵያ ፌዴራል ስርዓት የተዋቀረው ጎሳን መሰረት አድርጎ አይደለም። ለምሳሌ ደቡብ ክልልን ብንመለከት 56 ብሄር ብሄረሰቦች በአንድ የተካተቱበት ሁኔታ ሲኖር በተመሳሳይ በጋምቤላ ክልልም ስድስት የሚደርሱ ብሄር ብሄረሰቦች የገኛሉ፤ በአማራ ክልልም ሁለት ወይም ሶስት ብሄሮች እንዲሁም በትግራይም ሁለት ወይም ሶስት ጎሳዎች ይገኛሉ። በአንድ ጎሳ ብቻ የተዋቀረ

ክልል የለም። ሁሉም ክልሎች ብዘሃነት የሚታይባቸው ናቸው። በየትኛውም ክልሎች ቢሆን ብሄር ብሄረሰቦች ራሳቸውን የማስተዳደር ሙሉ መብታቸው የተጠበቀ ነው።

**ጥያቄ፣** በአንዳንድ የአውሮፓና አሜሪካ አገሮች የሚታየው የወቅቱ የኢኮኖሚ አለመረጋጋት በኢትዮጵያ ላይ ያስከተለውን ተፅእኖ እንዴት ይገመግሙታልያዩታል?

**ጠ/ሚ-** በእበርግጥ በእነዚህ አገሮች የነበረው የኢኮኖሚ መቀዛቀዝ አንዳንድ ጥሩ ጎኖች የነበሩት ቢሆንም በታዳጊ አገሮች ኢኮኖሚ ላይ ብዙ አሉታዊ ነገሮችንም አስከትሏል። ለምሳሌ በእነዚህ አገራት በተከሰተ የኤኮኖሚ መቀዛቀዝ ምክንያት ለውጭ ንግዳች በምናቀርባቸው እንደ ቡናና ወርቅ ዋጋ ላይ ከፍተኛ ቅናሽ ታይቷል። በተመሳሳይ ወደነዚህ ገበያዎች የምንልካቸው የአበባ ምርቶቻችን ላይም ከፍተኛ የዋጋ ቅናሽ በመከሰቱ ተጎድተናል።

አብዛኛው የአፍሪካ አገር የኢኮኖሚ እድገት ውስጣዊ በመሆኑ እነዚህ አገሮች በኢኮኖሚ ቀውስ ውስጥ ሆነው እንኳን 5%ና ከዚያ በላይ በሆነ እድገት ማስመዝገብ የቻሉበት ሁኔታም ነበር።

**ጥያቄ፣** በምስራቅ አፍሪካ አገሮች ህብረት መካከል በጣም ጠንካራ ግንኙነት አላቸው ቢሆንም እንዲህ ያለውን ቀጠናዊ ግንኙነት ኢትዮጵያ በጥንቃቄ ነው የምትምለከተው። ይህን ጥንቃቄ የተሞላበትን ፖሊሲ አሁንም የምትቀጥሉበት ይሆናል?

**ጠ/ሚ-** የውጭ ፖሊሲያችን ትኩረት የሚያደርገው በጎረቤት አገሮችና በምስራቅ አፍሪካ አገራት ላይ እንደሆነ አውቃለሁ። በቀጣይ የአፍሪካ አገሮች የኢኮኖሚ ትስስራቸውን በማጠናከር ወደ ፖለቲካ ውህደት ይሄዳሉ። በዚህ ራዕይ የእያንዳንዱ አገር የባህልና የታሪክ ልዩነት አፍሪካን ከኢኮኖሚና ፖለቲካ ውህደት ሊያግዳት

አይቻለውም። አብዘሃነት እንደ መልካም ነገር በመውሰድ ለጥንካሬአችን ምንጭ ይሆናል እንጂ ለልዩነታችን ምንጭ መሆን የለበትም።

በኢትዮጵያ እንኳን ብዙ የባህልና የብሄር ልዩነቶች ይስተዋላሉ። ይሁንና እንደ አገር የምንጋራቸው ብዙ መልካም ነገሮች አሉ። ለምሳሌ፣ ቅኝ ገዥዎችን በጋራ መከላከል በመቻላችን፤ ቅኝ አልተገዛንም፤ ይህም የሚያመጣው አለም አቀፍ የአስተሳሰብ ለውጥ አስከትሏል። እነዚህ ነገሮች እንደተጠበቁ ሆነው እኛ በአብዛኛው አፍሪካዊ ባህል ያለን በመሆኑ የሚያመሳስሉን ነገሮች ይበዛሉ። የጋራ የሆኑት ነገሮች ወደ በቅድሚያ ወደ ኢኮኖሚያዊ አንድነት ብሎም ወደ የፖለቲካ ውህደት ያመሩናል። ኢትዮጵያ የምስራቅ አፍሪካ አገሮችን በኢኮኖሚያዊ ጥቅሞች ማለትም በመንገድ፣ በባቡር፣ በሃይል፣ በንግድ እንዲሁም በባህል ለማስተሳሰር ከሁሉም ቀድማ እየሰራች ትገኛለች።

**ጥያቄ፣** ሰፋ ባለ ደረጃ እንየውና፣ ከጎረቤት ሀገሮች ጋር ያላችሁን የፖለቲካ ግንኙነት ምን ያህል ወደ ዴሞክራሲ ስርዓት ግንባታ፣ ዕድገት እንዲሁም ድህነትን ማጥፋት ደረጃ ለማሳደግ ጥረት አድርጋችኋል?

ጠ/ሚ- ይህች አገር ልታድግና ልትለማ የምትችለው ድህነትን ማጥፋት ስንችል ብቻ ነው። ዋናውና ቀዳሚው ጉዳይ ይኸ ነው። በኢትዮጵያ ፈጣን የኢኮኖሚ እድገት ሊመዘገብ የቻለው የዴሞክራሲ ስርዓትን መተግበር በመቻላችን ነው። እንደ ኢትዮጵያ ባሉ የብሔር፣ የጎሳ፣ እንዲሁም የሃይማኖት አብዘሃነት ባለበት አገር የሁሉንም ፍላጎት ማጣጠም የሚችለው ዲሞክራሲያዊ መንግስት መመስረት ሲቻል ብቻ ነው። ለዚህ አንድ ምሳሌ ላንሳ በከፍተኛ ትምህርትና በሙያ ማሰልጠኛ ተቀሞቻችን ከሚሊዮን በላይ ተማሪዎች አሉን። እነዚህ ተማሪዎች የተለያየ ዳራና ፍላጎት ያላቸው በመሆናቸው የሁሉን ፍላጎት ሊያሟላ የሚችል ዴሞክራሲያዊ የሆነ አስተዳደር መመስረት ባንችል ኖሮ የአገሪቱን አንድነት ማስቀጠል አንችልም ነበር።

የአገራችን መልክዓ ምድራዊ አቀማመጥ ያለመረጋጋት ባለበት የአፍሪካ ቀንድ አካባቢ ነው፤ ይህ ቀጠና ደግሞ ለአሸባሪዎች ለጥቃት የተጋለጠ ነው። በቅርቡ

በኬንያው ዌስት ጌት የገበያ አደራሽ የደረሰው ጥቃት እንዲሁም በአዲስ አበባ የተቃጣውና የከሸፈው የሽብር ጥቃት ተጠቃሽ ናቸው።

በአንድ በኩል አገራችንን ከጥቃት ለመከላከል እንዲቻል የአሸባሪዎችን እንቅስቃሴ በጥንቃቄ መከታተል ሲኖርብን፣ በሌላ በኩል ደግሞ የህዝቦቻችንን ሰብአዊና ዴሞክራሲያዊ መብቶች ማክበርም ይኖርብናል። ስለዚህ እነዚህን ሁለት ነገሮች በጥንቃቄ ጎን ለጎን ማስኬድ ካልቻልን በቀጠናው ሰላም ሊመጣ አይችልም።

**ጥያቄ፣** የአረቦች አይነት የፀደይ አብዮት ወደ አፍሪካ ይመጣል ብለው ያስባሉ? ወይስ ከሰሃራ በታች ያሉ አገራት ይህን አይነት ጎዳና አልፈዋል ብለው ያስባሉ?

**ጠ/ሚ-** እንደሚመስለኝ ሁሉም አገራት የየራሳቸው የተለያዩ ተጨባጭ ሁኔታዎች አሏቸው። ከላይ ለማንሳት እንደሞከርኩት አፍሪካ ወጣቶቿን በአግባብ መያዝ ካልቻለች (የስራ እድል መፈጠር ካልቻለች) የአረቦች ፀደይ ወደ አፍሪካ መምጣቱ አይቀርም። አሁን ላይ ሆነን ስናየው የአረቦች አብዮት በመጨረሻ የተቆናጠጡት አክራሪዎችና አሸባሪዎች ናቸው። በመሆኑም በእንዲህ ያለ ሁኔታ የሚካሄዱ ለውጦች ወዳልታሰበ መንገድ እንዳይሄዱ በጥንቃቄ መያዝ አስፈላጊ ነው። ሰዎች ሁሌም በአንድ አቅጣጫ ብቻ ማሰብ የለባቸውም፤ ግራና ቀኙን ማየት አስፈላጊ ነው።

**ጥያቄ፣** በቅርቡ የቀድሞውን አፍሪካ አንድነት ድርጅትን እና የአሁኑ የአፍሪካ ህብረት ሃምሳኛ አመት የምስረታ በዓል ተከብሯል። አፍሪካ ህብረት የተጣለበትን ሃላፊነት በአግባቡ ተወጥቷል ብለው ያምናሉ? በአባል አገራት መካከል የአመራር ችግር እንዳለም የሚጠቁሙ ትችቶች በተከታታይ ይደመጣሉ። ይህን ጉዳይ በተመለከተ የእርስዎ አስተያየት ምንድ ነው?

**ጠ/ሚ-** የአፍሪካ ህብረት ውድቀት አጋጥሞታል የሚል እምነት የለኝም። የአፍሪካ አንድነት ድርጅትም የአፍሪካ አገራት ከቅኝ ግዛት እንዲላቀቁ ትልቅ አስተዋፅኦ አበርክቷል። የአፍሪካ አንድነት ድርጅት በደቡብ አፍሪካ የነበረውን የዘር መድልኦ እንዲወገድ ትልቅ ስራ ሰርቷል። አሁን ደግሞ የአፍሪካ ህብረት አካሄዱን በመቀየር በአፍሪካ ያሉ ግጭቶችና የሰብአዊ መብት ጥሰቶች እንዳይከሰቱ እየሰራ ነው። በዚህ ጉዳይ ዙሪያ ሁሉም የህብረቱ አባል አገራት መስማማት ላይ በመደረሳቸው በአህጉሪቱ ትልቅ መሻሻል ታይቷል። ለአብነት ያህል በሶማሊያ ሰፍኖ የነበረው ስርዓት አልበኝነት የአፍሪካ አገራት በወሰዱት እርምጃ ትልቅ መሻሻል እያሳየ ነው። በአፍሪካ ይታዩ የነበሩ ግጭቶች እየቀነሱ በመምጣታቸው የአፍሪካ አገሮች የኢኮኖሚ እድገት እያስመዘገቡ የመጡበት ሆኔታዎች አሉ።

እነዚህ ሁሉ ነገሮችን የሚያስተባብረውና የሚመራው የአፍሪካ ህብረትና በሌሎች ተቋሞች እንደ NEPADን በመጨመር ነው። ይህን ስል ግን አፍሪካ ህብረት ሁሉንም አላማውን አሳክቷል ማለት አይደለም ብዙ የሚቀሩ ነገሮች አሉ። የብዙ ሀገሮችንና የብዙ ቡድኖችን ድርጅቶች ውህድ የሆነ ድርጅት በመሆኑ ከችግሮች ሊፀዳ አይችልም።

**ጥያቄ፣** በሄግ የሚገኘው የአለም አቀፉ የወንጀል ችሎት (International Criminal Court) በአፍሪካ ብዙ ጊዜ የመነጋገሪያ ጉዳይ ሆኗል። ይህ ተቋም በአፍሪካ የፖለቲካዊና የማህበራዊ ፍትህን መለኪያ ስለመሆኑ የእርሶ አስተያየት ምንድነው?

**ጠ/ሚ-** የአለም አቀፉ የወንጀል ችሎት በምህፃረ ቃል ICC እየተባለ የሚታወቀውን ተቋም ህጎችና አተገባበሮቹን በቅድሚያ መረዳት ተገቢ የመስለኛል። የተቋሙን ህጎች በተመለከተ ምንም ተቃርኖ የለንም፣ ምክንያቱም ህጎቹ ከህግ በላይ መሆንን ለመከላከልና የዘር ማጥፋት ወንጀልን ለመካላከል ተብለው የተደነገጉ ናቸው። እነዚህ ጠቃሚ የሆኑ ህጎችና መመሪዎች እና በአፍሪካ ህብረት በራሱ ተዘጋጅተው የህብረቱ መተዳደሪያ ላይ ከመካተታቸውም በላይ በአባል አገሮች ህገ መንግስት ውስጥ እንዲካተቱ ተደርገዋል። ከዚህ መረዳት የሚቻለው የአፍሪካ አገሮች ከICC ህጎችና መመሪያዎች ጋር ተቃርኖ የሌለን መሆኑን ነው።

ከቅርብ ጊዜያት ወዲህ ከICC ጋር ያለመግባባት የተፈጠረው በእነዚህ ህጎችና መመሪያዎች ሳቢያ ሳይሆን በአፈፃፀማቸው ላይ በሚታይ ችግር ሳቢያ ነው። ይህን ስል ሁሉም የICC ህጎች አተገባበር ላይ ችግር አለ ማለት ሳይሆን አንዳንድ ጉዳዮች ግን የግልፅነት ችግር ይታይባቸዋል። ICC ለተመሳሳይ ነገሮች ተመሳሰሳይ እርምጃ ሲወስድ አልታየም ወይም ለተመሳሳይ አፈጻጻሞች ተመሳሳይ መለኪያዎችን ባለመጠቀሙ የተቋሙ አሰራር ወጥነት ይጉረው እንላለን።

እኛ አፍሪካዊያን እያልን ያለነው በመንግስታቱ ድርጅት (UN) ውስጥ አፍሪካ ወሳኝ ቦታ (Veto Power) ሊኖራት ይገባል፤ ምክንያቱም አፍሪካ ከ1.2 ቢሊዮን በላይ የሆነ ህዝብ ባለቤት የሆነች አህጉር በመሆኗ ነው። የፀጥታው ም/ቤት ICCን የሚመራው ከሆነ አፍሪካም ተወካይ ይኖራታል ማለት ነው።

ይህን የምናገረው እንደ አፍሪካ ህብረት አባልነቴ እንጂ እንደ ኢትዮጵያ መሪ ሆኜ አይደለም፤ ምክንያቱም አገሬ የICC አባል አገር አይደለችምና። በርግጥ ከግማሽ በላይ የሆኑት የአለማችን አገራትም ICC አባል አገር አይደሉም። በተመሳሳይ ሃያ የሚደርሱ አፍሪካ ህብረት አገራትም ICC አባል አይደሉም። አፍሪካ በራሷ የፍትህ ስርዓት ልትተማመን ይገባታል፤ አፍሪካ ነፃ ነች ማለት የሚቻለው የራሷን ጉዳይ ራሷ ማየት ስትችል ነው። ይህን ማድረግ ካልተቻለ አፍሪካ ነፃ ነች ማለት አይቻልም።

*Source : NewAfrica Magazine 48th year January 2014. No 535*